# አወልያ፣ ዋልድባና ኢትዮ ኤርትራ

## የ”ሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ” ዘማሪዎች ሰሞንኛ ዳንኪራ

**ዮናስ** 3/26/12

ሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ /zero sum game/ መርህ አይነተኛ መገለጫ የዜሮ ድምር ፖለቲካ አስተሳሰብ ነው፡፡ ዋና ግቡ ደግሞ ሥርዓትን መለወጥ፣ መንግስትን መገልበጥ ነው፡፡ የሚበዙቱ የፖለቲካ ልሂቃን እንደሚሉት አለም ወደ አንድ መንደር እየተለወጠች በምትገኝበት በዚህ ወቅት፣ ለሃገራት የርስ በርስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትሥሥሮሽ ዴምክራሲያዊ ሥርዓት እጅጉን ወሣኝ በሆነበት በዚህ ሰዓት የመንግሥትን ሥልጣን ማግኘት የሚቻለውና ሥርዓቱ መንግስት ማዋቀር የሚቻለው በምርጫ ብቻ እንዲሆን አስገድዷል፡፡ ከዚህ ውጪ በሚደረግ የትጥቅ ትግልና መፈንቅለ መንግስት እንዲሁም ወታደራዊ ሥልት ስልጣን ላይ የሚወጣ መንግስት ፈተናዎቹ ብዙ ናቸው፡፡

አንድ ሀገር እንደሀገር ለመቀጠልና መንግስት ህዝቡን በአግባቡ ማስተዳደር እንዲቻለው ለአለም አቀፍ ህጎች ተገዢ መሆንና በኢኮኖሚ ትሥሥሮሽ ውስጥ ተዋናይ የመሆኑ ጉዳይ የውዴታ ግዴታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ከዴሞክራሲያዊ ምርጫ በመለስ ሥልጣን የሚቆናጠጡ መንግስታት ደግሞ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ከሚደርስባቸው መገለል ባሻገር በህዝባቸው ዘንድ የሚኖራቸው ተቀባይነት ባዶ ስለሚሆን እንዲህ አይነት ሥልጣን የመያዣ መንገዶች እያከተመላቸው ይመስላል፡፡ስልጣንን በጡንቻ የሚመርጡ ጥቂት መንግስታትን በተለይም የአፍሪካ መንግስታትን ለአብነት ብናስታውስ የምንረዳውም ከላይ የተጠቀሰውን የመገለል ያለመረጋጋትና የመተራመስ ሃቅ ነው፡፡

በሌላ በኩል የትጥቅ ትግልና መሰል አማራጮች ጉዞ ረጅም ከመሆኑ የተነሣ ጭቆናን ሳይሆን ስልጣንን መሠረት አድርገው ለሚነሡ ሃይሎች የሚዋጥ አማራጭ አይደለም፡፡ የነዚህ ሃይሎች ፍላጎትና መነሻ ህዝብ ሳይሆን ሥልጣን በመሆኑ ረጅሙ ዳገት ያንገፈግፋቸዋል፡፡ ህዝብን መሠረት ላደረገ ሃይል ግን ወሳኙ አላማ ነውና ትግሉ የሚፈጀውን ጊዜ ይውሰድ እንጂ ጨቋኝ የሆነውን ሥርዓት ለመለወጥ ጽናት ይኖረዋል፡፡

የተለየ ፍላጎት ያላቸው የውጭ ሃይሎች ደግሞ ፍላጎት ባሳዩበትና ፍላጎታቸውን ለማሳካት ካነጣጠሩበት ሀገር ምላሹ እምቢታ ሆኖ ከተገኘ የሚወስዱት አማራጭ ከነዚሁ በአቋራጭ ሥልጣን ለመረከብ ከሚቋምጡ ሃይሎች ጋር አብሮ መስራትን ነው፡፡ ዓላማቸው ወቅታዊ ፍላጎታቸውን ማሳካት እስከሆነ ድረስ ደግሞ በሂደት በሚገኝና በምርጫ ከሚመጣ ሥልጣን ጋር መወዳጀት

አይፈልጉም ፍላጎታቸው ዛሬን ቢያልፍ የቅርብ ጊዜ ስለሚሆን የሚጋልቡትን ፈረስ ከቋመጡት ሀገር ይመለምላሉ፡፡ ፈረሡም ለስልጣኑ፤ ጋላቢውም ለፍላጎቱ ሲል አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆን አብረው ይሰራሉ፡፡ ዓላማቸው ወይ ሁሉን ማግኘት ነው ወይ ሁሉን ማጣት ነው፡፡ ከፊል ወንበር ፣ የህዝብ ድምፅ፣ ህገመንግሥት፣ ምርጫ ቦርድ ወዘተርፈ ለነሡ በሚጠቅም ወይም ሁሉንም ከማግኘት ቅኝት አንፃር እስካልሆኑ ድረስ ለነሱ እስር ቤቶች ናቸው፡፡ ይህ ነው የዜሮ ድምር ፖለቲካ፡፡

ወደዋናው አጀንዳዬ ለመግባት የዜሮ ድምር ፖለቲካን ወይም የሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ ማስፈጸሚያ ታክቲክ በተመለከተ የቅርብ ጊዜ ትዝታችንን በማሳያነት ባቀርብ ነገሬን ግልጽ ያደርግልኛል፡፡

ምርጫ 97ን ለአፍታ እናስታውስ፡፡ መጀመሪያ ወደቅድመ ምርጫው፡፡
በምርጫ ህግጋትም ሆነ በምርጫ ተፈጥሮ እንደፓርቲ አሸናፊ ሆኖ ለመገኘት አብዛኛው የፖለቲካ ስራ የሚከወንበት ሰዓት ነው፡፡ ከቅስቀሣ ጀምሮ ፕሮግራምን ማስተዋወቅና የምረጡኝ ዘመቻው እጅግ አድካሚና ፈታኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ዋነኛ ተዋናይ የሚሆኑት ምርጫ ቦርድ፣ መንግስት፣ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችና መራጩ ህዝብ እንደሆኑም ይታወቃል፡፡

በቅድመ ምርጫ 97 ውቅት የምናስታውሳቸውና የዛሬውም ዳንኪራ መቺዎች እነ ብርሃኑ ነጋ፣ መስፍን ወልደማርያም፣ ነጋሶ ጊዳዳ፣ መራራ ጉዲና እና በየነ ጴጥሮስ ያኔም ንቁ ተሳታፊ የነበሩ ሲሆን ወደ ኋላ ግን የተረጋገጠውና የተደረሰበት ነገር ግለሠቦቹ በምርጫ ሽፋን ሲጓዙ የነበረው በሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ መርህ ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ሥልጣን ለመጨበጥ ከነበራቸው ጽኑ አቋምና ጥማት በመነሳት በራችንንና ገመናችንን ምንም ለማይመለከታቸው የውጭ ሃይሎች በርግደውት ነበር፡፡በታዛቢ ሽፋን በተበረገደው በር የገቡት እነ አና ጎሜዝና ቲምክለርክ ደግሞ ትዝብቱን ወደጎን በመተው የጆርጂያ እና ዩክሬንን ታሪክ ለመድገም የሞት ሽረት ትግል አድርገዋል፡፡ ታሪክ እራሱን ሁሌም ላይደግም ይችላልና አልሳካ ሲላቸው የጎዳና ላይ ነውጥ ይነሳ ዘንድ በትሮይ ፈረሶቻቸው ላይ ኮርቻውን ጫኑ፡፡ ምንም እንኳን መደምደሚያው የሚያሳዝን ቢሆንም የዜሮ ድምር ፖለቲካ አስተሳሰብ በመሠረቱ ወይ ሁሉን ማግኘት ወይ ሁሉን ማጣት ነውና ያገኙትን ከፊል ወንበር በመተው ሁሉን ማጣትን መርጠዋል፡፡ ዳሩግን ብዙዎች ወጣቶችን ደግሞ ሠለባ አድርገዋል፡፡

እነ አና ጎሜዝ እና ፈረሦቻቸውም፣ ምርጫው ተጭበርብሯል፣ መንግስት ያለምርጫም ቢሆን ሥልጣን ለታቃዋሚዎች ማጋራት አለበት፣ ኢትዮጵያ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ የምታገኘውን እርዳታ ልታጣ ይገባል፣ የሚሉና መሰል ለዓላዊነቷን ጭምር የሚጋፉ ሁኔታዎች በሀገራችን ላይ ይፈጠር ዘንድ ሳይታክቱ ቢሰሩም ይህም ውጤታማ ሳይሆን ቀረ፡፡

የቀለም አብዮትንና የሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ መርሆን ቀድሞ የተገነዘበው መንግስት ህገመንግስታዊ ስርዓቱ በሃይል እንዳይናድ  በጥንቃቄና በትጋት በመስራቱ ህዝቡም የተቃዋሚውን ጎራ ሴራ እየተረዳና በምክንያት መደገፍንና መቃወምን በመልመዱ የተጋለጡት ጋላቢዎችና ፈረሶቻቸው በመጋለጣቸው ጋላቢዎቹም ወደመጡበት ፈረሶቹም ወደ ጋጣቸው በመግባት የመጀመሪያው ዙር ሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ እሩጫ ተጠናቀቀ፡፡

በይቅርታ ከጋጣቸው የወጡት ፈረሶች  እርስ በርስ መነታረክና መወነጃጀል የመጀመሪያ ተግባራቸው ሆነ፡፡ ይህ ደግሞ ያልተሳካ የዜሮ ድምር ፖለቲካ መሠረታዊ ባህርይ ነው፡፡ ቀጠለናም ግሚሱ ፓርቲ አቋቋመ፣ ከፊሉ ተሰነጣጠቀ ዋናው ፈረስ ደግሞ ወደ ጋላቢዎቹ መንደር በማምራት የሽብር ፖሊቲካ ፓርቲ አቋቋመ፡፡ ግን አሁንም እርስ በርስ መነካከስ፣ መሰዳደብና መዘላለፍ ዋነኛ መገለጫቸው እንደሆነ ነው፡፡ እዚህ ሲሉት እዚያ የሚገኝ አመራር፣ በፓርቲው ስም ማታ አንዱ ያወጣውን መግለጫ ጠዋት አንዱ ሲያፈርሰው ፣አንዱ ለመዋሃድ ሲሰራ ሌላው ለመፈረካከስ ሩጫው ቀጥሏል። ሁሉም ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ በአንድነት እንደተሰለፉ ናቸው፡፡

ምርጫ 2002 ደረሰና በዝረራ ቢሸነፉም ያው በተለመደ ማላዘን "ምርጫው ተጭበርብሯል" የሚለውን ለማስከተል በማሰብ "ምርጫው ነጻና ዴሞክራሲያዊ መሆኑ ላይ ስጋትና ጥርጣሬ አለን" የሚለውን መፈክር ያሰሙት ግን ገና ከምርጫው አስቀድሞ ነበር፡፡ መንግስት በአንድ በኩል ይህን ህጋዊ የሚመስልና ህገወጥ አካሄድ እየተከላከለ በሌላ በኩል ደግሞ የጀመረውን ልማት ለማሳካት ያደረገው ጥረት የተሳካ ሲሆን እነዚህ ሃይሎች ዳግም እንደገና በአደባባይ ተጋለጡ፡፡ አሁን በ97 ምርጫ ወቅት ተከስቶ የነበረው ዓይነት ግርግር እንዳልተደገመ፣ ሌላው ቀርቶ እንዳልታሰበ፣ቢሞከርም ኖሮ እንኳ አንዳች ነገር ጠብ ሊል እንደማይችል የተረዱት ፈረሶች ሁሉንም ለማግኘት ወይ ሁሉንም ለማጣት የታክቲክ ለውጥ አደረጉ፡፡

ፕሬሱን፣ ኤምባሲውን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ጎረቤት ኤርትራን በመያዝ “ሰብአዊ መብትና ፍትህ” የሚል ታርጋ አድሰው ለጠፉ፡፡ ከዚያም የጋምቤላ ኢንቨስትመንት፣ የፕሬስ አዋጅ፣ የመያዶች አዋጅ፣ እንዲሁም የግብር ከፋዮች ምዝገባና አዲስ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ወዘተና በስተመጨረሻ ላይም የሊዝ አዋጅ  ዋነኛ ማምታቻና ማደናገሪያቸው ሆኑ፡፡ አዋጆቹ ደንቦቹና መመሪያዎቹ ኢንቨስትመንቱንም ጨምሮ ለህዝብ ጠቃሚ ስለመሆናቸው ሳይታክት ግንዛቤ ላስጨበጠው መንግስት ጉዳዩን እንዳመጣጡ በማስተናገዱና ህዝቡም በተጨባጭ ተጠቃሚ መሆኑን በማረጋገጡ አሁንም እነዚህን ሃይሎች "ለሽ በሉ"  አላቸው፡፡

ይኼ ካልተሳካ ደግሞ ያሉት እነዚህ ፀረ ሠላም ሃይሎች አጥፍቶ መጥፋትን አማራጭ በማድረግ አሁን ደግሞ ስስና ቀልብ ገዥ (Sensitive) ናቸው ብለው ባመኑባቸው ሃይማኖታዊ ጉዳዮችና የጋራ በሆነው የሉአላዊነት ጉዳይ ዳግም ተመልሰዋል፡፡ የአወልያ፣ ዋልድባና የኢትዮ-ኤርትራ ሰሞንኛ ጉዳይ አዲሱ ዳንኪራቸው ሆኗል፡፡

ሰሞንኛ አጀንዳ ከነበረው የእስልምና እምነትና አማንያን ልጀምር፣ በየብዙሃን መገናኛዎች የወጡት መረጃዎች ሁሉ በአማንያኑ መካከል ለተነሳው ፀብ መንስኤ ነው ሲሉ ያቀረቡት፦ መጅሊሱ ወይም እስልምና ምክር ቤቱ በምርጫ ያልተሰየመና ህገወጥ ነው የሚል ክስ በአወልያው ኮሚቴ በመቅረቡና በሌላ በኩል  ደግሞ መጅሊሱ ኮሚቴው ወሃቢያ በተባለ ጽንፈኛ አስተምህሮ የተጥለቀለቀና የዚህ አስተምህሮ ዓላማም ዞሮ ዘሮ ማጠንጠኛው እስላማዊ መንግስት በሃይል ማቋቋም ነው በማለቱ ነው፡፡

በርግጥም በአወልያው ኮሚቴ ውስጥ የተሰባሰበው ሃይል የወሃብያ ሠለባ የመሆኑንና ዓላማውም በሃይማኖት ሽፋን ድብቅ የፖለቲካ ጥያቄ ወይም የሥልጣን ጥያቄ መሆኑን በተጫበጭ ማስረጃ ደርሼበታለሁ ያለው መንግስት ጉዳዩ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የመግባትና ያለመግባት ሳይሆን ሉዓላዊነትን የማስከበርና የህዝብንና የሃገርን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ፤ከዚህም ጋር የዜጎችን የሃይማኖት ነጻነትንና እኩልነትን በሕገ መንግሥቱ መሰረት የማክበርና የማስከበር ጉዳይ በመሆኑ እነዚህን ሃይሎች ከድርጊታቸው ይታቀቡ ዘንድ አሳስቧል፡፡ በዚህ ያላበቃው መንግስት የህገወጦች እንቅስቃሴ ተገትቶ፤ ችግሮች አሉ ከተባለ እንኳ በሃይማኖቱ አሰራርና መጅሊሱ በሚመራበት ሕገ ደንብ መሠረት በሰላማዊ ውይይት መፍታት እንደሚቻል ምክር ሰጥቷል፤ የሆነውም ይህ ነው፡፡

ለነመድረክና  ፍኖተ ነፃነት እንደዚሁም ፍትህ ለተሰኙ ፕሬሶች ነገሩ ሁሉ ጥብስ ነው። በፊት በአዲስ ነገር በኩል ለመፈፀም የሞከሩትን ህገወጥ አካሄድ አሁን ደግሞ በነፍትህና ፍኖተ ነፃነት እየቧቸሩበት ነው። "መንግስት በሃይማኖት መሃል ጣልቃ ገብቷል" በሚል በሌላ ጉዳይ ላይ የሚያጣጥሉትን ህገመንግስት በመጥቀስ ለሕገ መንግሥቱ መርሆዎች መከበር ዋነኛ ተቆርቋሪዎች መስለው በመቅረብ አሁን ደግሞ የራሳቸውን ስውር ፖለቲካዊ አጀንዳ ለማሳካት ሊጠቀሙበት እየሞከሩ ነው። ጉዳዩ ሃይማኖትና የእምነት እንደመሆኑ አማንያንና የሃይማኖት አባቶች ደግሞ ስለእምነታቸው ያላቸውን አቋም የሚገነዘቡት ከእነዚህ ሃይሎች  ድብቅ አላማ ባሻገር በመሆኑ መንግስትን በዚህ ጉዳይ ላይ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከማስከበር አኳያ ጉዳዩን አጽንኦት በመስጠት እንዲከታተለው ሲሉ ወትውተዋል። የህ ደግሞ በምንም መልኩ በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ተደርጎ የሚወሰድ አይሆንም፤አይደለምም፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ስላለመግባቱ ይልቁንም ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ የህዝቡን ደህነነት እያስጠበቀ እንደሆነ እነመድረክ በውስጣቸው ጠንቅቀው ቢያውቁትም የሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ ተፈጥሮ ነውና  ጭር እንዳይል ታክተዋል። ዳሩ ግን ይህም አልሆነላቸውም። በታሰበው መሰረት ጉዳዩ እልባት እያገኘ መሆኑን ሲረዱ በፍጥነት የታጠፉት ወደ ዋልድባ ገዳም ነው።

አሁን ያለውን የስኳር ፍጆታ ውስንነት በዘላቂነት ለመፍታትና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት መንግስት ለመገንባት ካቀዳቸው ግዙፍ የስኳር ፕሮጀክቶች መካከል የዋልድባን ገዳም ከከበቡት ወንዞች አንዱ በሆነው የዛሬማ ወንዝ ላይ የሚገነባው የወልቃይት ስኳር ልማት ፕሮጀክት አንዱ ነው።

በትግራይ ክልል በሚገኘው ወልቃይት ወረዳ ላይ የሚካሄደው ይህ ፕሮጀክት 25 ሺህ ሄክታር መሬት የሸንኮራ አገዳ የሚለማበት ሲሆን በቀን 10 ሺህ ቶን አገዳ የሚፈጭ ፋብሪካ የሚገነባበት ነው።

በዚህ ፕሮጀክት የሚፈጠረውን የስራ እድል እንኳ ትተን ያለብንን የስኳር እጥረት በማስወገድ በኩል ፕሮጀክቱ የሚኖረውን ፋይዳ ስናይና እጥረታችን ለሆነው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ያለውን አስተዋፅኦ ስንመለከት ተስፋ መሰነቅና በማናቸውም መልኩ ድጋፍ ማድረግ ከኛ የሚጠበቅ ነው። ሆኖም እነዛ ተጋልበው ተጋልበው አወልያው ላይ አርፈው የነበሩት ሃይሎች አንዳንድ የዋልድባ ገዳም መነኮሳትን ጥቅማችሁ ሊነካ ነው ፣ ገዳማችሁ ሊፈርስ ነው ብለው በማነሳሳት ማጯጯኋቸውን ቀጥለዋል። የምርጫ 97ን የትርምስ አቅጣጫ ሲያራግቡ የነበሩት ቪኦኤና መሰሎቹ ዋልድባንም ዋነኛ አጀንዳቸው
አድርገውት ዳንኪራ ሲመቱ ከርመዋል።

በነገራችን ላይ ቪኦኤና መሰሎቹ በአወልያውና መጅሊሱ መካከል በነበረው አለመግባባት ላይ ቤንዚን ሲያርከፈክፉ የነበረ ሲሆን፤ ወሃቢያን በገንዘብ ሲደግፉ የነበሩ የቀለም አብዮተኞች ያኔ በታዛቢ ካባ ምርጫ 97 ላይ ነበሩበት። አሁን ደግሞ የሰብአዊ መብት በርኖስ ደርበው በዋልድባ ጉዳይ እጃቸውን ሰደዋል። ፈረሶቻቸውም ሰምሶማ ላይ ሳሉ ሌላ "ጥብስ የሆነ አጀንዳ" የተገኘ በመሆኑ እንደለመዱት አሁንም በፍጥነት ወደኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ በመታጠፍ ዳንኪራ እየመቱና እስክስታ እየወረዱ ነው።

በሌላኛው የጥፋት ኃይሎች የማዘዣ ሰፈር ደግሞ የኤርትራ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በኢትዮጵያ የሽብርና የማተራመስ ስትራቴጂን እንደስልት እየተከተለ የተለያዩ ፀረ ሰላምና ጠብ ጫሪ ድርጊቶችን መፈፀሙና አሁንም በመፈፀም ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ባለፈው አመት አጋማሽ ላይ የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ በነበሩት ቀናት የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ |ሰላምና መረጋጋት የለም´ የሚል ምስል ለመፍጠርና ጉባኤውን ለማሰናከል ፀረ ሰላም የሆኑ የኢትዮጵያ ተላላኪዎችን በመጠቀም አዲስ አበባ ውስጥ ለመፈፀም ያሴረው የሽብር ድርጊት ሳይሳካ መክሸፉም የሚዘነጋ አይደለም።

አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ ´ በሚል መርህ ወታደራዊ ስልጠና አስታጥቆ ወደ አገር ውስጥ የላካቸው እነዚህ የፀረ ሰላምና የሽብር ሃይሎች ሊፈፅሙት የነበረው የሽብር ጥቃት ቆይቶ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኤርትራና የሶማሊያ ሁኔታ አጣሪ ቡድን ባካሄደው ጥናት ጭምር ተረጋግጧል።

በዚህ ዓመትም በተመሳሳይ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ የኤርትራ መንግስት ተላላኪዎቹን በመጠቀም በቅርቡ በአፋር ክልል በጉብኝት ላይ በነበሩት ቱሪስቶች ላይ በወሰደው የሽብር ጥቃት አምስት ቱሪስቶች ተገድለው ሌሎች ደግሞ ታግተው ከቆዩ በኋላ መለቀቃቸው የሚታወስ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው አህጉራዊው ጉባኤ ከመካሄዱ አስቀድሞ በኤርትራ መንግስት ተላላኪዎች አማካኝነት የተፈፀመው የዚህ ሽብር ተግባር አላማም የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት ለማወክና የአፍሪካ ቀንድን የግርግር አደባባይ ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የሽብር ጥቃቱ በተፈፀመበት ሰሞን የኤርትራ መንግስት ከዚህ መሰል የሽብርና የፀረ ሰላም ተግባሩ የማይታቀብ ከሆነ ኢትዮጵያ ተመጣጣኝ እርምጃ በመውሰድ ራሷን እንደምትከላከልም ገልጾ ነበር።

በዚሁ መሰረት የኤርትራ መንግስት ለተላላኪ ሃይሎች ወታደራዊ ስልጠና የሚሰጥባቸው ማእከላት ላይ ጥቃት ፈጽማለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ዛሬም ይሁን ነገ በሁለቱ ተጎራባች አገሮች መካከል ያለው አለመግባባት በድርድር ይፈታ ዘንድ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ከኤርትራ መንግስት ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆኗንም እያስታወቀች ነው።

እንግዲህ ሃቁ ይህ ነው። የተለያዩ አለም ዓቀፍ ሚዲያዎችም ቢሆኑ የኤርትራንና የመንግስቷን አዋኪነት ጠንቅቀው የተገነዘቡት ዛሬ ሳይሆን ቀደም ብሎም በመሆኑ የኢትዮጵያን ራሷን የመከላከል ርምጃ በመደገፍ በዘገባዎቻቸው አመልክተዋል። በርካታ አለም አቀፍ ዘገባዎች ኤርትራን የኮነኑበትና የኢትዮጵያን እርምጃ ትክክለኛነት የተገነዘቡበት፣ አለያም ሃገራትና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ቢያንስ ለኤርትራ ባዶ ጩኸት በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ዝምታን በመምረጥ ምላሽ የሰጡበት አካሄድ ሲጤን ኢትዮጵያ የምትታወቀው በፀረ ሽብር አቋሟ እንጂ በትንኮሳ ላለመሆኑ ግልጽ ማመላከቻ ነው።

ሆኖም የኤርትራው መስታወቂያ ሚኒስትር ለውጭ ሚዲያዎች በተለይም ለቪኦኤ የአማርኛው አገልግሎት በሰጡት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ መንግስት ያጣቸውን ሰላምና የውስጥ ችግር ለማስቀየስ የወሰደው እርምጃ ነው ሲሉ ፣ የዞሮ ድምር ፖለቲካ ተፈጥሮ በመሆኑ ይህንኑ የአሊ አብዶን ንግግር ተቀብለው ያስተጋቡት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና ባልደረቦቻቸው ናቸው። ዳሩ የተሰበረው ምሽግ የነ ኢሳያስና የነነጋሶ የጋራ ቤት በመሆኑ ይህን ቢሉም አይደንቀንም። ግን ጥያቄዬ እስከመቼ ነው በሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ መርህ የሚጓዙት?የሚለው ነው። አሁን የኢትዮጵያ ራስን የመከላከል ጥቃት ያስበረገጋቸው ኤርትራና ተላላኪዎቿ እዚህና እዚያ ዳንኪራ እየመቱ ሲሻቸውም ሙሾ እያወረዱ ነው። በጋራ ነጋሪት የሚመቱበትን ቦታ ደግሞ ያመቻቹ ይመስላል። በአንድ እንትትን እንትትን እንዳላልን አይነት ነገር ነጋሶና አሊ አብዶ አንድ ነገር ይዘው እያንጎላጁ ነው። ዳሩ ሁሉን

ማግኘት ከባድ ነው ሁሉን በማጣት መዝለቅ ደግሞ ሁሌም የሚቻል አይመስለኝም። መቆም ያለበት ጋር መቆም ይገባዋል።